# ይድረስ ለበጋሻው ደሳለኝና መሰል የሣጥናኤል ደቀ መዛሙርት

ዳግማዊ ጉዱ ካሣ (ከአዲስ አበባ)

## መከፊቻ

እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለቅዱሣን ስለማይስማማ፣ **ዝሙት ወይም ማናቸውንም ዓይነት ርኩሰት ወይም ንፍገት ማድረግ ይቅርና ወሬው እንኳ ሊሰማባችሁ አይገባም**፡፡ ይልቅስ ለእግዚአብሔር ምሥጋና አቅርቡ እንጂ **የሚያሣፍርና ዕርባና የሌለው ወይም ጸያፍ ነገር መናገር አይገባችሁም**፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ነገር ለእናንተ ተገቢ አይደለም፡፡ **አመንዝራም ቢሆን፣ ማናቸውንም የርኩሰት ሥራ የሚያደርግ ቢሆንም ወይም ጣዖት አምላኪ የሆነ ንፉግም ቢሆን፣ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት እንደማይኖረው ዕወቁ፡፡**

**በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ስለሚመጣ ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ**፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ ከማይታዘዙ ሰዎች አትተባበሩ፤ እናንተ ራሳችሁ ቀድሞ በጨለማ ውስጥ ትኖሩ ነበር፤ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ውስጥ ስለሆናችሁ በብርሃን እንደሚኖሩ ሰዎች ኑሩ፡፡ ምክንያቱም የደግነት ሁሉ፣ የጽድቅና የእውነት ፍሬ የሚገኘው ከብርሃን ነው፡፡ **ስለዚህ ጌታን ደስ የሚያደርገው ነገር ምን እንደሆነ መርምሩ፡፡ ወደ ብርሃን አውጥታችሁ አጋልጡት እንጂ ፍሬ ቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥጋ ጋር አትተባበሩ፡፡ እነርሱ በሥውር ስለሚያደርጉት ነገር መናገር እንኳ ያሣፍራል**፡፡ ሁሉ ነገር ወደ ብርሃን ሲወጣ እውነተኛ መልኩ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡ …(ለተጨማሪ ግንዛቤ ኤፌሶን 5 ከቁጥር 1 ጀምረህ ዝለቀው)

እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ፡፡ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ እላለሁ፡፡ ምክንያቱም የሥጋ ምኞት ከመንፈስ ምኞት ጋር ተቃራኒ ነው፤ መንፈስና ሥጋ እርስ በርስ ይቃረናሉ፤ ስለዚህ እናንተ የምትፈልጉትን ማድረግ አትችሉም፡፡

**የሥጋ ሥራዎች የታወቁ ናቸው፡፡ እነርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነትና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው**፡፡ … **እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡**

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ደግነት፣ በጎነት፣ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡ … (ለበለጠ ግንዛቤ ገላትያ 5 ከቁጥር 16 እስከ ማብቂያው፤ ድምቀትና የግርጌ መስመር ከኔው የተጨመረ)

(በቀድሞው የአያ ጨቡዴ የደርጉ ዘመነ መንግሥት ጊዜ እንዲህ ሆነላችሁ - ለትውስታ ያህል፡፡ የያኔው ፓትርያርክ አቡነ ተክለሃይማኖት በ80ዓ.ም ይሞታሉ፡፡ ኮሚኒስቱ መንጌ ሆዬ ሥርዓቱን የማይጎረብጥ ሌላ ፓትርያርክ ለመሾም በየክፍለ ሀገሩ ጳጳስ ፈልጉ ይላል፡፡ ተፈልጎም አልቀረ - ይገኛል፡፡ “ከወዴት አገኛችሁ?”ብሎ ባለሟሎቹን ሲጠይቅ “ከትግራይ” ይሉታል፡፡ ትግራይ ደግሞ ዳግማዊ ወያኔን አፍርታ ራስ ምታት ሆናው ነበር፡፡ በዚያም ሳቢያ “ከዚች ክልል የሚገኘው የመንግሥት ገቢ ለክልሉ ጠመኔ መግዣም አይሆንም!” እያለ በ“ወይኒቱ እኮ ገና አልበሰለችም” ዓይነት የቀበሮዋ ሥነ ልቦናዊ ራስን የማታለያ ዘዴ መንጌ ራሱንና ሕዝቡን የሚያታልልበት ወቅት ነበር - አባባሉም ሆነ አመለካከቱ የተሳሳተና መንጌን ከመሰለ “በሳል” መሪ የማይጠበቅ ነበርና፡፡ ብቻ ዕጩው ጳጳስ ማለትም ፓትርያርክ ከትግራይ መገኘቱን እንደሰማ አጅሬ በንዴት ፎግልቶ “ምን ማለታችሁ ነው ጓዶች! እንዳመጣብኝ እኔው ደርቤ እይዘዋለሁ እንጂ ብላችሁ ብላችሁ ከትግራይ ታመጡብኝ?” አላቸው ይባላል፡፡ እኔም ቢጨንቀኝ አለፈናየ በሃይማኖቱ ገብቼ ላምቧትር ነው፡፡ ምን ላድርግ? በሁሉም መጫወቻ ሆነን ቀረን እኮ፡፡ በውነት አለመታደል ነው፤ የማንም ውርጋጥ ከሃዲ ይፈንጭብን ጓዶች?)

እህሳ! ወንድም በጋሻው ደሳለኝ ይህችን ለየት ያለ ቃና ያላት ጦማር ማንበብ ስትጀምር ምን ተሰማህ? ሞቀህ ወይንስ በረደህ? የበግ ለምድህን ለብሰህ በጎች መሀል በመመሸግ ለሥጋህ ምኞት ስትል የምታደርገውን ነገር ሁሉ እኛ የማናውቅ መስሎህ ይሆን? ግዴለህም ሕዝቡም ዛፍና ቅጠሉም ያውቃል፡፡ ነገር ግን በላዩ ላይ ያረበበበት ወያኔያዊ አፍዝ አደንግዝ ተብትቦ ስለያዘው እንኳንስ ያንተን ሰይጣናዊ ተፈጥሮ ተረድቶ አንቅሮ ወደመትፋት እርምጃ ሊገባ ይቅርና ታላቁን የአራት ኪሎ የአጋንንት ምሽግ ለማፍረስም አቅም አጥቶ ኤሎሄ እያለ ነው፡፡ ዙሪያው ገደል የሆነበት የተወሰነው የማኅበረሰብ ክፍል አንተን የደገፈ መስሎ ስላጨበጨበልህ በአባትህ የጥልቁ ጨለማ ንጉሥ ትዕቢት ተነፍተህ የምትሠራውን እንዳጣህ በስፋ መነገር ይዟል፡፡ እንዳንተ በትዕቢት ያበጠ አንድ የቀድሞ ዘመን ንጉሥ በሕዝብ መሀል ራቁቱን መሆኑን የነገረው አንድ ሕጻን ልጅ ነበር አሉ - ሌላውማ ልክ አንተን ከብቦ አፉንም በመዳፉ ለጉሞ በውስጡ እየሣቀና ለይምስል እያጨበጨበልህ በድንቁርናህም እያፌዘብህ እንደሚገኘው ምዕመን የያኔውም ጀማ ለንጉሡ ክብርን የሚሰጥ ነበር የሚመስል፡፡ … ቢሆንም ታናናሽ ልጆቹ የምናውቀውን እንናገራለን - እስከዚያውም ቢሆን፡፡

የዐውደ ውጊያን ብዛት ለመቀነስ ስንል ብዙ ዜጎች በአንድ አቅጣጫ ብቻ - ብዙውን ጊዜ በፖለቲካው ላይ - ስናተኩር በሃይማኖቱና በኢኮኖሚው ሕዝባችንን የሚያማስኑትን እንደነበጋሻው ያሉ ሥጋበል ሐሳይ መሢሆችንና የቢዝነስን “ሀሁ” የማያውቁ ስግብግብ ነጋዴዎችን እንረሳቸዋለን፡፡ ይሄ ሞልቶ የማይሞላ ከላስቲክ የተሠራ ሆድ ስንትና ስንት ጉድ በሀገራችን ያሳየን ይዟል፡፡

በግሌ ስለዚህ የሰይጣን ደቀ መዝሙር ብዙ ነገር እሰማለሁ፡፡ የምሰማው ነገር ደግሞ ከተራ የምቀኞች መንደር ሳይሆን ከሁነኞች ነው፡፡ ዛሬ ግን አንድ የፌስቡክ ጦማር አነበብኩና በሽታየ ተነሳ፡፡ ዝም ማለትም አቃተኝ፡፡ “ስትናደዱ አትጻፉ” የሚሉ አንዳንድ ቅንጡ ጸሐፊዎች ሊቀየሙኝ ቢችሉም ካልተናደድኩ የምጽፈው ነገር አይመጣልኝምና በመናደዴ ምክንያት መጻፌ ነው፡፡

በቅድሚያ ይህችን አጭር ታሪክ እነሆ፤ መቼ፣ የትና ከማን እንደሰማኋት ዘነጋሁ፡፡

አንዱ በጉን ሊሸጥ ገበያ ይወጣል፡፡ በሚፈልገው ዋጋ ሊሸጣት ግን አልቻለም፡፡ ብዙ ቀን ይንከራተታል፡፡ እርሱ አሥር ብር ሲል ገዢዎች ወደ አምስትና ሦስት ብር እያወረዱበት ክፉኛ ይቸገራል፡፡ ጊዜው ዱሮ መሆኑን ልብ በሉ ታዲያ - ቆዳ መልስ በሁለት ብር በግና ፍየል በሚበላበት ዘመን - ኧረ እንዲያውም በአምስት ብር የገዛሃትን በግ ቆዳዋን አሥር ብር ልትሸጥና ተከፍሎህ ሥጋ የምትበላበት አጋጣሚም ሞልቶ ነበር! ያ ሰውዬአችን ታዲያላችሁ በጊቱን "በማይረባ ዋጋ ከምሸጥ ለምን አርጄ እኔ ራሴው ከነቤተሰቤ አልበላትም" በማለት ሃሳቡን ይለውጥና አርዶ ሥጋዋን በመብላት አንጋሬውን( ቆዳዋን) ሊሸጥ ወደ ገበያ ይሄዳል፡፡ ገበያ ሲሄድ ከገበያው ዳር ጀምሮ ሊገዛው ያሰፈሰፈው ሁሉ የተለያዩ ዋጋ እየጠራ ያማልለው ይይዛል፡፡ በመጨረሻም ጭራሽ ከጠበቀው ውጪ በሆነ ከፍተኛ ዋጋ ሸጦ ይመለሳል - ሃያ ብር ግድም፡፡ ይሄኔ ሰውዬው ከመገረሙ የተነሣ "ለካንስ በጌን ያረከሰብኝ ሥጋዋ ኖሯል ?" አለ ይባላል፡፡ ትልቅ አነጋገር! ለሁላችንና በተለይም ለዚህ ክፉ ዘመን ተለክቶ የተሰፋ ግሩም ሰም ለበስ ቅኔ፡፡

አዎ፣ የሥጋ ገበያ እንዲህ ነው፡፡ ሥጋ የነፍስን ጥንካሬ ያዝላል፤ መንፈስን ያደክማል፤ ኅሊናን ይሠውራል፡፡ መላ አካልን ያበሰብሳል፤ አእምሮን ያነቅዛል፡፡ ሥጋ ከሰውነት ተራ ያወጣል፤ የትልቅ ትንሽም ያደርጋል፤ ያዋርዳል፡፡ የሥጋ ገበያ ዕድል በከፈተልህ የማጭበርበሪያ መንገድ እየገባህ ሥጋህን እንድታደልብ መንገዱን ያመቻችልሃል፡፡ በፖለቲካው በለስ ባይቀናህ በሃይማኖቱ፣ ሃይማኖቱ ቢያደናቅፍህ በንግዱ፣ ንግዱ ባይሣካልህ በጥንቆላና በመተቱ፣ በዚህና በዚያ ባይሆንልህ በዝርፊያና በለየለት ሙስና እንዲሁም በስርቆት ... ለጊዜው እንድትምነሸነሽ የዕድል በሮችን ሁሉ እስከጥግ ያምቦረቅቅልሃል - ልክ እንደነበጋሻውና መሰሎቹ፡፡ የነሱ ምናልባት ከዚህም ባለፈ ልዩ ዲያብሎሣዊ ተልእኮም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ማን ያውቃል - ኢትዮጵያን ከሃይማኖቱ አንጻር ውሉ የጠፋበት ልቃቂት በማድረግ መቅኖ አጥታ እንድትቀር የሚፈልጉ የውጭ ታሪካዊ ጠላቶችና የውስጥ ቅጥረኞቻቸው አሰልጥነው ልከውትም ሊሆን ይችላል፡፡ ለነገሩ ወዲያም አለ ወዲህ ማዕከላዊ መንስኤው ያው ሥጋ ነው - ሥጋን ለማደለብ ከሚደረግ ጥረት የሚመነጭ የሀገርና የእምነት ክህደት ነው፡፡ ልደቱ አያሌው ገና ሮጦ ባልጠገበበት የልጅነት ዕድሜው ሀገሩን የከዳው ለነፍሱ ሣይሆን ለሥጋው ምቾት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለሥጋው ያደረ ሰው እንኳንስ ሀገሩንና ሃይማኖቱን የገዛ ነፍሱንም ሳይቀር ለጨለማው ገዢ ኃይል ገብሯልና ለማንም ለምንም የሚተርፍ አንዳችም የርህራሄ ስሜት የለውም፤ ማንንም ይሸጣል ፤ ማንንም ይለውጣል፡፡ በጥቅም የታወረ በመሆኑ መላ ዕውቀቱንና "ጥበቡን" የሚያውለው ለሰይጣናዊ ቁሣዊ ዕድገቱ ብቻ ነው - ልክ እንደነበጋሻው ደሳለኝና መሰል የሁለት ዓለም ጌቶች፡፡ ፈራጅ እግዚአብሔር ነው - አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ከሥራቸው አንጻር ሲታዩ - ፈጥነው በንስሃ ጸበል ካልታጠቡ በስተቀር - እነዚህ ሰዎች ለበስባሽ ሥጋቸው ሲሉ ጠፍተዋል፡፡

በበጋሻውና በመሰሎቹ እንዲህ የምትወርደባቸው ምን አድርገው(ህ) ይሆን የሚል ጥያቄ ሲነሣ ይታየኛል፡፡

ቀጣዩን የበጋሻውን ስብከት ተመልከቱ፡፡ ለዝርዝሩ ደግሞ ደጀኔ ሺፈራው (dejenie shiferaw/facebook/) በሚል አድራሻ ጎልጉሉና ጥቂት እንደተፌሳቦካችሁ እርግጡን ታገኙታላችሁ፡፡ በዚያ አጭር የፌስቡክ ጽሑፍ የዚህን የእፉኝት ልጅ እውነተኛ ተልእኮ ታገኛላችሁ፡፡ (ይህችን ጽሑፍ ከመጀመሬ ጥቂት ቀደም ብሎ ከአንድ ዲያቆን ጋር ስለዚህ ሰው ክፉ ተፈጥሮ ሳወራ ‹ይህ የእፉኝት ልጅ› ስል ሰማኝና እርሱ ደግሞ ቀበል አድርጎ ‹ምን የእፉኝት ልጅ ትላለህ - ራሱ እፉኝት ነው እንጂ!› ቢለኝ ጊዜ በስሜቶቻችን መናበብ ገረመኝ፡፡) ለማንኛውም ወዳስገራሚው ስብከቱ -

"...ዝሙት፣ ስካር፣ ስርቆት፣ ማጨስ... ችግር የለውም፡፡ ይህ የሥነ ምግባር ችግር እንጂ የሃይማኖት ችግር አይደለም፡፡ ..."(ምንጭ - የደጀኔ ሽፈራው የፌስቡክ ገጽ)

"መጋቤ ሀዲስ ዲያቆን" በጋሻው አታላይ - ማለቴ ደሳለኝ - ሆይ! "ባናርስ አጣምደናል" ይላል የሀገሬ ጨዋ፡፡ ከየትኛው መጽሐፍ ነው ይህን "ቃለ ሕይወት" ያገኘኸው እባክህን? አንተን ለማወቅ ይህ ጽሑፍ ብቻ በቂ ነው፡፡ ከበቂም በላይ፡፡ በተነገረው ያልተነገረውን ማየት ይቻላልና፡፡ ይህ ቅንጣቢ የስብከትህ አካል የሚያስተላልፈውን መልእክት ለመረዳት ብዙ መማርና መመራመርም አያስፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ፍርድህን እስኪሰጥህ ድረስ እውነተኛ ማንነትህን እነግርሃለሁ፡፡ አንተ አድምጥ፡፡ በአካል የምንገናኝበትም ዘመን ብዙም ሩቅ አይመስለኝም - ያኔ የዚህን የሀፍረተቢስነትህንና ሃይማኖት የለሽነትህን መንስኤ ትነግረኛለህ - ለነገሩ ይህ ስብከትህ ሃይማኖት አፍራሽነትህን ብቻ ነው የሚጠቁመው - እንጂ ሃይማኖት የሌለው ሰውማ እስከዚህን አይወርድም፡፡ የወደቀ ግንድ ምሣር እንደሚበዛበት ሁሉ አንተም በበኩልህ ይህንን የዋህ ሕዝብ እንዲህ ትጫወትበታለህ፡፡ ፈጣሪ ፍርዱን እንደሚሰጥህ ባልጠራጠርም እስከዚያ ግን እውነቱን የመናገር ኃላፊነትና ግዴታም አለብንና የዚህን እባብ ሰውዬ ሤራና የተንኮል ተልእኮ የምናውቅ ወገኖች አለመታከት ማጋለጥ እንደሚኖርብን ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡

እናም አንተ በጋሻው ሆይ! የክርስቶስ አገልጋይ ሳትሆን ዓለምንና መላውን ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ሀብቷን ለመቆጣጠር የሚቋምጡት የምሥጢራዊ ድርጅቶች (secret lodges) ልዑክ ነህ፤ እርግጥ ነው አንተ የተልእኮህን መሠረት ላታውቀው ትችል ይሆናል፡፡ ይሁንና ከተግባርህ በመነሣት የአንተነትህን ተፈጥሯዊ አድራሻ መጠቆም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ጠንቋይ መቀለብ ሳያስፈልግ በፍሬያቸው ይዘት ምንነታቸው የሚታወቁ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህ ኢሉሚናቲ በመባል የሚታወቁ የሉሲፈር መንግሥት(New World Order) ሥውር አንቀሳቃሾች ኢትዮጵያን ቀርቶ ሌሎች ዓለማትን(ምድርን በዋናነት ጨምሮ) ለመቆጣጠርና በበላይ አለቃቸው በሣጥናኤል ግዛት ሥር ለማዋል ያልፈነቀሉትና የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ሆሊውድና ቦሊውድ ሁሉም -ውዶች የነሱ ናቸው፡፡ በነዚህ የሙዚቃና የፊልም ኢሞራላዊና ኢሃይማኖታዊ ኢንዱስትሪዎቻቸው ያችን የ666 የመጨረሻ ዘመነ መንግሥት እውን ለማድረግ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደርሰዋል፤ አንተ የምትሰብክላቸው መጠጥና ወሲብ እንዲሁም ስርቆትም የነሱ መዋቢያ ጌጣቸው ናቸው - የሕጎቻቸው የማዕዘን ራሶች፡- በወሲብ ከፈለጉት መዳራት፣ መጠጣትና መስከር፣ መስረቅና ሥጋህ ያዘዘህን መፈጸም አንተው እንዳልከው በነሱ ችግር የለውም ብቻ ሣይሆን የሚፈቀድ ነው - የማይፈቀደው ይልቁናስ እነዚህን የሥጋ ፍላጎቶች አለማድረግ ነው፡፡ አንተም እንግዲህ አወቅኸውም አላወቅኸውም የነሱ አባል ነህ ማለት ነው፡፡ ይህን የምልህ በድርጊትህ እንጂ ትከተለዋለህ በምትባለው የእምነት ቅርንጫፍ(denomination) አይደለም - ተሃድሶ ምናምን ስትባል መስማቴን በገደምዳሜ መጠቆሜ ነው፤ የሆንከውን ሁን - መብትህ

ነው። ነገር ግን በተለይ ወጣቱ የእግዚአብሔርን መንገድ ሣይሆን የኢሉሚናቲዎችን የጥፋት መንገድ እንዲከተልና እንዲጠፋ በምታደርገው ሰይጣናዊ ስብከት የተነሣ የሰይጣን ቤተ አምልኮ አባልነትህን በድፍረት አረጋግጠህልናል፤ አሳውቀኸናልም፤ የምታመልከው ሣጥናኤል አብዝቶ ይባርክህ።

ለመሆኑ ስድስተኛውና ሰባተኛው የአሥርቱ ትዕዛዛት ሕጎች ምን ይላሉ? ዳሩ ልቦናህ በገንዘብ ሥክሮና ጭንቅላትህ በአጋንንታዊ ትምክህት ተወጥሮ እንዴት ታስታውሰዋለህ? ለማንኛውም እነዚያ ሕጎች "አታመንዝር" እና "አትስረቅ" የሚሉት ናቸው። ታዲያ ዝሙትና ስርቆት በክርስትና ሕይወት ችግር የማይኖራቸው በየትኛው ስሌትህ ይሆን? ምን ነካህ ወንድማለም? ይህ ስብከትህ እኮ "ዐወቀች፣ ዐወቀች ቢሏት የባሏን መጽሐፍ አጠበች" የሚለው ብሂል ከሚያስተላልፈው የቂልነት መልእክት በእጅጉ የተለዩ ነው። እንዲህ ያለ ስብከት ሰይጣን ራሱም አይሰብከውም - ሰይጣን ካንተ የተሻለ ይሉኝታ ሳይኖረው የሚቀር አይመስለኝም፤ ይህንን ስልህ እኔ ካንተ የተሻለ እንከን የለሽ ስብዕና ኖሮኝ ሣይሆን የኔ የኃጢኣት ዕድፍ ጠንቁ ከኔ ባለፈ ሌሎችን እምብዝም የማይጎዳ ሲሆን ያንተ ግን ተሰሚነትህን በመመርኮዝ የኃጢኣት ብስናትህን በብዙዎች ዘንድ ትዘራዋለህና ያ ክፉኛ አሳስቦኝ ነው፤ ሰይጣን ደግሞ እንዳንተ ታዋቂና በየመስኩ በተለይም በስብከት፣ በመዝሙር፣ በዘፈንና በኪነ ጥበብ ዘርፍ አንዳች ተሰጥዖ ያላቸውን ሰዎች አሳድዶ ነው ምርኮው የሚያደርጋቸው። ለምሳሌ "ባህታዊ" እንትናን ያኔ በ80ዎቹ እኩሌታ ሰይጣን በደምብ የተጠቀመበት እኔን መሰሉ ጎጋ ዜጋ በጭፍን እየተከተልነው የክርስቶስን ያህል - እንዲያውም በበለጠ - ክብርና ዝናን ስላጎናጸፍነው ነበር። አጅሬ ሰይጣንም በዚያ በገብረ መስቀል ሰውነት ውስጥ ገብቶ ብዙዎችን አሰናከለ፤ አሳ(ሳ)ተ። ከሜዳ ተነስቶ ንጹሕን ሰው ስቅሎ ስቅሎ የሚልና ከቀየው ባሻገር ከአድማስ ወዲያ ማዶ ሌላ አገር ያለ የማይመስለው ተራ ዜጋ አንተን መሰሉን የጭቃ እሾህ ሰይጣን ሲልክበት እንዴት አይፈተን? በውነቱ እግዜር በኪነ ጥበቡ ይሁነን እንጂ ዘመኑ የከባድ ፈተናዎች ዘመን ነው። እናም የእምነት መስመርህ ምንም ይሁን ምን በሥራህ ግን የአባትህን የዲያብሎስን ግብር እየገለጥክ በመሆንህ ከዛሬ ጀምሮ የሣጥናኤል ደቀ መዝሙር መሆንህን ሁሉም እንዲረዳ በኀያው እግዚአብሔር ስም እጠይቃለሁ። አያውቁብኝም ብለህ ከምትገምተውና ከምታስበውም በላይ አቀውቀንብሃል፤ አውቀንሃልም። ጊዜውነን ተረዳው እንጂ ሊቀ ማዕምራን። ለነገሩ እኮ ዕውቀትን በሚመለከት ከእግዜሩ ቀጥሎ እንደሰይጣን ዐዋቂ አይገኝም፤ በማወቁም ነው ፈጣሪውን የተገዳደረው ይባላል። ስለዚህም በጋሻው ዐውቆ ዐውቆ ሲጨርስ እኛን እንደድንጋይና እንደግዑዝ ነገር ቆጠረንና ያደርገውን ብቻ ሣይሆን ይናገረውንም በማጣት ያቀረሸብን ጀመር። የሰው ጥጋበኝነት የሚለካው በአነጋገሩም ነው - አያ እንደልቡን መለስን አስታውስ፤ እንዳንተው ነበር። "ከተራብ ለጠገበ አዝናለሁ" መባሉም የጠገበ ለንግግሩ ቀርቶ ለድርጊቱም ድንበር ስለማያበጅለት ነው - የኋላ ኋላ ግን ትልቅ አደጋ አለው - ምናልባትም እስከ ንስሃ ግዛት የማያደርስ ከፍተኛ አደጋ። ከቻልክ አሁኑኑ ወደእውነተኛው የፈጣሪ መንገድ ብትመለስ ደስ ይለኛል።

ለነገሩ በጋሻው ያቀረሸብን። ሲያንሰን ነው። ለመጣ ለሄደው ሰብኣዊ ፍጡር እንሰግዳለን፤ መጽሐፍ የጠቀሰንና በአፈ ቅቤ ምላሱ አንጀታችን ውስጥ ገብቶ የሚነጠፍን የተግባር ድሃ ሁሉ ውስጡን ሳንመረምር በአፍ ጂዶ እየተጠለፍን በቀላሉ እንሸነፋለን፤ በአንዴ ልባችንንም ቆሽታችንንም እንሰጣለን። ምድረ አጭበርባሪ የሰይጣን መንጋን በከንቱ ውዳሤ ሰማየ ሰማያት ድረስ እናወጣቸዋለን፤ ፈጣሪን እየዘነጋን ለነሱ እናጎበድዳለን - ሲሰግዱለት የማይወድ ደግሞ የለም - እንኳንስ በኋላ ቀር ሀገር ባደጉትም ይህን በሰዎች ዘንድ የመመለክ ምትሃታዊ ኃይል ያሸነፈ የለም። በውሲኪና በጮማ እናቀማጥላቸዋለን፤ በኃጢኣት ያገኘነው(ያከማቸነው) ገንዘብ የሚታጠብ(cf. money laundering) እየመሰለን እነሱን ከማምነሽነሽ ባለፈም አብያተ ክርስቲያንን እናሠራለን - ሊያውም ድሃውን ያቺን ያለቿውን ጥንጥዬ ሣንቲም ዘርፈን ሙልጨን በማውጣት በምንመዘብረው ገንዘብ(ማሳነጻቸውን አልቃወምም፤ የምቃወመው አካሄዱን ነው - ፈጣሪ ደግሞ ያን ያህል ሞኝና እንደሰው በዋዛ የሚታለል አይመስለኝምና ይህ ዓይነቱ የታይታ ሥራ ከንቱ ነው)። መኪናና ቤት ሣይቀር እንገዛላቸዋለን - ገነት መግቢያ ካርድ የሚሰጡን ይመስል - የኢንደልጀንስ ካርድ በውድ ዋጋ ይሸጡ እንደነበሩት ልክ እንደመካከለኛው ዘመን አጭበርባሪ ካቶሊኮች - እኛም ፈጣሪን ጭራሽ ዘንግተን እምነታችንን በነሱ ላይ እንጥላለን። መንፈሣዊ ዐይናችንን ሞራ ሲጋርደው ሕገ እግዚአብሔርን ወደ ጎን እንተውና አንሶላ እስከመጋፈፍም እንጎዳኛቸዋለን፤ ከነሱ ጋር መተኛት መንግሥተ ሰማይን እንደመውረስ የሚቆጥሩ ሴቶች እንዳሉ መገመት አይከብደኝም። አንወሻሽ፣ እንደዚህ ዓይነት ሰንካሎች አሉ - ለበለጠ መረጃ ደግሞ እነ "እማሆይ" እጅጋየሁ ይጠየቁ። በተጨማሪም በሚስቶቻችን ጭኖች እየገቡ የተቀደሰውን ስንዴ ወደ እንክርዳድነት እንዲለውጡት በውጤቱም ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን የሚገባው ትዳራችን መቅኖ አጥቶ እንዲቀርና ቤተሰብ እንዲበታተን በሩን በርግደን እንከፍትላቸዋለን፤ ከዚያም በል ሲለን በኛው ብሶ እናማቸዋለን፤ እናሸሟጥጣቸዋለንም። ብቻ በጥቅሉ ከእግዜሩም በላይ እናነግሣቸውና የቤታችንም የደጃችንም አዛዥ ናዛዥ እናደርጋቸዋለን። ሥራቸውን ስንመለከትና ስንደርስበት ግን የምንገባበትን እናጣለን - አንዳንዶቻችን ደግሞ በሰከንድ ውስጥ ሃይማኖታችንን እንቀይራለን - ሸሚዝና ከናቴራ በምንለውጥበት ቅጽበታዊ ፍጥነት። ሃይማኖት መለወጥ ለመሠረታዊ የሕይወት ውጣ ውረድ ችግሮቻችን መፍትሔ ያመጣ ይመስል በእልህ የማናደርገውና የማንሆነው ነገር የለም። ብዙ ጉድ መዘከዘክ እችላለሁ። እናም ይገባናል - በልካችን የተሰፉ ናቸው። "ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይክፋሽ" ነው ነገሩ። ስሙን አንስቼ የማልጠግበው ልደቱም፣ በጋሻውም፣ በረከትም፣ አባ ጳውሎስም፣ መንግሥቱም፣ "ባህታዊ" ገብረ መስቀልም፣ ታምራት ገለታም፣ "በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከክርስቶስ አምስት ልጆችን ወለድኩ" እያለች ሕዝበ አዳምን ያነፈለለች ያቺ ቀጣፊ ሴትም፣ ሽመልስ ከማልም፣ ገነት ዘውዴም፣ ሣዓረም፣ ሣሞራም፣ አባ ናትናኤልም፣ አባ ግርማም፣ ሣምሶን ማሞም፣ ሙሉጌታ አሥራተ ካሣም፣ ሠራዊት ፍቅሬም፣ ኃይሌ ገ/ሥላሤ(ም፣) በመንታ ያለቀሰለት መለስ ዜናዊም፣ ውብሸት ወርቃለማሁም፣ አላሙዲንም፣ ሶሎሞን ተካልኝም፣ አባመላም(ብር. ዳ.)፣ አለምነህ መኮንንንም፣ ገዱ አንዳርጋቸውም፣ ክፍሌ ወዳጆም፣ … ዘተፀውዓ ወዘኢተፀውዓ ስሞሙ - ምን አለፋችሁ እኚህና መሰሎቻቸው የዲያቢሎስ ጭፍሮችና የሰንበት ጽንሶች ሁሉ - በክፉ ሥራችን ሰበብ እኛኑ ለመቅጣት ሲባል ተፈጥሮና ፈጣሪ "ተመሳጥረው" የላኩብን የመከራና ስቃይ አምባሳደሮች ናቸው፤ እነዚህ ክፉ ልጆቻችን በተለይም በሕይወት ያሉት የቁም ተዝካራችንን እያወጡልን እንደሆነ ያህል ይሰማኛል። ብዙ የምናወራርደው ዕዳ ሣይኖርብን የሚቀር አይመስለኝም። የላቲኑ ቅዳሤ mia colpa, mia colpa, mia grandissima colpa, የሚሉ

ሐረጋት አሉት፤ "በኔ ጥፋት፣ በኔ ጥፋት፣ በኔ ትልቅ(ብዙ) ጥፋት" እንደማለት ነው፡፡ ልክ ነው - "በኛ ጥፋት፣ በኛ ጥፋት፣ በኛ ትልቅ ጥፋት" ይህ ሁሉ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መቅሰፍትና ውርጅብኝ ተልኮብናል ብዬ በግሌ አምናለሁ፡፡ ልባዊ የሆነ ጸሎት ያስፈልገናል፡፡

ምን እናድርግ? ታዲያ ጥፋቱ የነበጋሻው ብቻ ነው ወይንስ የኛም ጭምር? እኔ እንደሚመስለኝ የመጣውን ሁሉ በአብዛኛው ወደን በፈቃደኝነት የምንሸከመው እኛው ነን፤ በጋሻው ለአንድ የዐውደ ምሕረት ስብከት ሃያ ሺህ ብር ስጡኝ ሲል ከሰጠነው ያባላግነውና በነፃ የተቀበለውን መክሊት በውድ ዋጋ እንዲሸጥ፣ አላግባብም እንዲከብርና የመንፈስ ቅዱስን በረከት እንዲርቅ ያደረግነው እኛም ጭምር እንጂ እሱ ብቻ አይደለም፤ አደራውን እንዲበላ ያደረግነው እኛው ነን - ይህ ስህተታችን በሁሉም ዘርፍ ይታያል፤ ከፉኛ እየጎዳንም ይገኛል፡፡ ሙብቱን በርካሽ የሚሸጥና በግዴታው ላይ የሚያለምጥ ዜጋ በብዛት የምናገኘው በሀገራችን ነው ብንል ብዙም አንሳሳትም - ቤቱን ከፍቶ የሚሄድ ሰው ደግሞ በሌባ መማረር የለበትም፡፡

እንዲያው ለመሆኑ በዚህ በገንዘብ ጣጣ የተነሣ የስንቶች ፍቱን ጠበሎች የፈዋሽነት ኃይል ደብዛው ጠፍቶ የለምን? አሁን አሁን እኮ የእምነቱ ምልክቶች ጥርኝ ብርኝ እያሉ ይታዩ እንደሆነ እንጂ እምነትማ ከናካቴው ጠፍታ የለም እንዴ? በዚህ የሆድ አምላኪዎች ዘመን የመስቀል ቡራኬ እንኳን በገንዘብ እየተለወጠ ክህነትና መለኮታዊ በረከት ተቃቅረው በጎች በተኩላዎች እየተበሉና ተኩላዎችም ዘመን በጣለላቸው ግዳይ እየወፈሩ ይገኛሉ፡፡ ዕድሜ ለነበጋሻው ዘንድሮ ተኩላና ቀበሮ ተመችቷቸዋል፡፡ የነገውን አናውቅም፡፡ ነገ ሌላ ነውና፡፡

በምኒልክ ዘመን ጆሮው የደነቀረ በምኒልክ ሲምል ይኖራል እንደሚባለው ሆኖብኝ በፊት ጊዜ ይህን ሰው በሥራው እወደው ስለነበር እየቆዬ ስለሱ የሚባለውን ማመን አቅቶኝ እንጂ ስለበጋሻው ከምሰማቸው አንዳንድ ነገሮች አንጻር ቀደም ብዬ ነበር ማውገዝ የነበረብኝ - ለነገሩ በዘመነ ሰይጣን አንድን ሰው አወገዝከ አላወገዝከ ምን ለውጥ አለው? አባታቸው ትልቁን የሥልጣን ቦታ ይዞ በተለይ አሁን የዓለማችን አዛዥ ናዛዥ እርሱ ሆኗል፡፡ ግን ምንም ካለማለት ዘግይቶም ቢሆን አንድ ነገር ማለት ይሻላልና አሁን የምለውን በነፃነትና በእውነት እላለሁ፡፡ እውነት ደግሞ አንጻራዊ ናት ይባላል - የኔ እውት ካንተ እውነት ልትለይ ትችላለችና፡፡ ሆኖም ቢሆን ግን እውነት ሺህ ጊዜ አንጻራዊ ናት ትባል እንጂ መሠረታዊ ሚዛኗን አትለቅም፤ ከዚህ አኳያ አንጻራዊ የሚባል እውነት የለም ወደማለት ልናዘነብል ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ሞተ ብንልና አልሞተም ብንል እውነቱ ባለበት ስላለና ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በአንዴ እውን ሊሆኑ ስለማይችሉ ሽክማችን የማጣራት ጉዳይ እንጂ የእውነት አንጻራዊነት እዚህ ላይ ሊሠራ አይችልም፡፡ ሞቶ የሚኖር ወይም እየኖረ የሚሞት የለምና - ከኢትዮጵያውን ውጪ ማለቴ ነው፤ በቁም ሞተን የምንኖር እኛ ብቻ ነን - እንደውሻ ኖረን እንደሰው የምንሞትም እኛው ብቻ ነን፡፡ አቤት እንዴት እንደምንኖር በተለይ የውጪዎቹ ወገኖቻችን ብታዩልን!

"በጋሻው ለአንድ የዐወደ ምሕረት ስብከት እስከ ብር 25000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) ይጠይቃል፤ በጋሻው ከሰው ኮርጆ መጽሐፍ አሣትሟል፤ በጋሻው ገናን በመሰሉ የፆም ወቅቶች ለስብከት የሚኮናተሩትን ሰዎች እንዲያርዱለት ነግሮ በቢራና በውስኪ እያወራረደ በድብቅ ይበላል፤ በጋሻው ከእነእንትና ጋር ይማግጣል፤ በጋሻው ብዙ እላፊ ስብከት - ማለትም ከቃለ ዐዋዲውና ከቀኖናው ያፈነገጠ ህፀፅ የተሞላበት ስብከት - ያካሂዳል፣ በጋሻው አንደበቱ ዘርፍጥ ነው፤ በጋሻው በኩራት ይለጠጣል፤ በጋሻው ራሱን እንደክርስቶስ ይቆጥራል፤ በጋሻው ..." የማልሰማው የለም፡፡ የሚሰማ ሁሉ ግን እውነት እንዳልሆነ እረዳለሁ - መጠርጠር ደግ መሆኑንም ጭምር፡፡ ምክንያቱም ፈረንጆቹ '"There is no smoke where there is no fire." የሚሏት ተገቢ አባባል አለቻቸውና እኛም "ጠርጥር ገንፎም አለው ስንጥር" እንላለንና እውነቱን ለማግኘት አጥብቆ መመርመሩ አይከፋም፡፡ የበጋሻው ሰይጣንነት እንዲህ በአደባባይ ጎልቶ ሲወጣ ግን የተባለውንና የሚባለውን ብቻም ሣይሆን ከዚያም ባለፈ ብዙ ጉድ እንደሚሠራ መረዳት አይከብድም፡፡ በአደባባይ "ዘሙቱ ፣ ስረቁ ችግር የለውም"የሚል ጀግና? ግን ከእውነት ምን ነካው?

ክርስቶስ ባዶ እግሩን ወይም ምናልባት በነጠላ ጫማ ከማንም አንድም ወሮታ በግዳጅ ቀርቶ በቃል-አልባ የዐይነውኃ ተማጥኖ ሳይቀበል የእግዚአብሔርን መንግሥት ለሦስት ዓመታት ከሩብ ገደማ ሰብኮ ስለእውነት ሲል በመስቀል ተቸንክሮ አለፈ፡፡ የርሱን መንገድ የተከተሉ ጥቂቶች ቢሆኑም እንደነበሩ በሃይማኖቱ ታሪክ ይወሳል፡፡ የአሁኖቹ ሃሳይ መሲሆች ግን የሚከረፉ ወንጀላቸውንና የሚቀረና ኃጢአታቸውን በክርስቶስ ስም አለአንዳች ሀፍረት በላያችን ላይ ይከምሩብን ገቡ፡፡ እነዚህ የእናት አባታቸው ገዳዮች የሆኑ የእፉኝት ልጆች እንዴት እንደሚኖሩ፣ እንዴት ባለ መኪና እንደሚሄዱ፣ እንዴት እንደሚለብሱ፣ እንዴት እንደሚጫሙ፣ እንዴት እንደሚሽቀረቀሩ፣ እንዴት እንደሚዝናኑ ... በማየት ብቻ ዕጣ ክፍላቸው ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል አስረግጦ መናገር ይቻላል፡፡ "አትፍረድ ይፈረድብሃል"ን ለጊዜው ተዋት፡፡ "ከዐይኔ በላይ" አለች አሉ ማናት...

አዎ፣ የሰይጣኑ አሸከር በቀላሉ ይታወቃል፡፡ ሀገራችን በተለይ በአሁኑ ወቅት የሰይጣኑ ማኛሪያ ሆናለች፤ ሌላው ዓለምም ጭምር፡፡ በሃይማኖቱ ዘርፍ እነቢጋሻውን የመሰለ አሰለጥ የአጋንንት ጭፍራ እንደማዛቱና ምዕመናንን እየሞለፈ ለቡታ ሣጥናኤል ግዛት አሳልፎ እንደሚሰጡ በንግዱም እነአላሙዲንን የመሰለ የቡታ ጣዖቱ ተገዢዎችን በሁሉቱ እያከበረ ዜጎችን ለነሰው እንዲሰግዱ እያደረገ ነው፡ ዛሬ ሴቱን ተመሞፍ ወንዱን አ– – ብሎ በሌው ከዚህ ሰይጣናዊ ትዕዛዝ ራሳቸውን የሚጠብቁ ዜጎች በጣም ጥቂቶች ናቸው – ምክንያቱም ዘመኑ የእርሱ ነውና! አንዲት ሰሚኘኛ አላሚዴናዊ ክስተት እንኳን ብፍይ ስሟ ማሪት የማስረፈልገኝ አንዲት ታዋቂ የከሀ ጥቡብ ሰው(ወጣት ናት) በብዙ ሚሊዮን ብር ቦሌ አካባቢ ግሩም ቤት አስገነብታለች አሉ – ይሄንኑ የአጋንንት ውለል በአትዮጵያ፡፡ በነገራችን ላይ አንዱ ሰዉዬ በቀደምለት "ይሄ ሰዉዬ ሴቶቻችንንና ልጆቻችንን በብሩ እያማለለ ጨረሳቸው፤ እግዜሩ ለኃጢአተኞች ስንት ዘመን ነው የሚጣቸው?" እያለ ፊጭርን ሲያማርር ሰማሁና በዚህ ቱጃር ዕድለኝነት እኔም ገረመኝ፡፡ የሰይጣኑ ገንዘብና ገና እንደነገም የሚሆን መሆኑ ከፋ እንጂ ልጅቱ ለጊዜው – ዕድሜ ለዚያች ሰው ለሰው ትያትር – እንኳንስ አስባው አልሞውም በማታውቀው ሁኔታ አልፎላታል፡፡

ይህ ሰዉዬ የሚፎክርበት ሀብት ግን የሕዝበ ሀብት ነው – ራቁቱን የተወለደ የሰው ፍጡር እንደምሁ ከየት አባቱ ሊያመጣው ይችላል ዱቢስ? የዓለም ሕዝበ ሀብት ነው፡ ጥቂቶች የሚያሽሽሉበት በቢሊዮንና በትሪሊዮን የሚቆጠረው የዓለማችን ሀብትና ጥሪት በፍትሃዊ መንገድ ብንጠቀምበት ኖሮ አንዱ በቁንጣን እየሞተ ሌላው በርሀብ በጠኔ አያልቅም ነበር፡፡ ዓለማችን የኢ-ፍትሃዊነት መድረክ ናት፡፡ ከጠቅላላው የዓለማችን የሕዝበ ብዛት አንጻር አንድ መቶኛ የሚሆኑ ዜጎች በሀብት ወደደር እስከ 79.2 ቢሊዮን ዶላር እያከማቹ አንዱ ለብ ቱጃር ከሌልኛው አጫርባሪና ደም መጣጭ ቱጃር ሰውደሩ 99 መቶኛው ሕዝበ ግን በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎችና በርሀብ እንዲሁም የሀብት ክፍፍሉ ኢሚዛናዊነት በፈጠረቸው ግን ልዩ ልዩ ልብሶች በሚጣጣቸው ጦርነቶችና የድንበር አካባቢ ግጭቶች አሜካይነት እየተረፈረፈ ነው፡ ይህ ጠማማ አካሄድ የተመሰረተው የሚጠገፈው በሰይጣናዊያን እንጂ በእግዚአብሔራዊያን ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡ ... ድግቱ ሀሉም ሟቾ፡፡ ዓለምን የዛሬ አንድ ወይም ሁለት መቶ ዓመታት በኋላ ምን ልትመስል እንደምትችል አስቡት፤ አንተም ከእንግዲህ ግፋ ቢል ስንት ዓመታትን እንደምትኖር አስበው፡ ሞት ደስ አያልም? አዎ፣ ሞት አስተካካይ ነው፤ እርጅና አስተካካይ ነው፤ በሽታ አስተካካይ ነው፡፡ ከሁሉም ከሁሉም ያለን የሌለ የሚያደርግ አጅሬ ሞት ባይኖር ኖሮ እንደዓለማችን ፍትህ አልባነት ምን ይውጠን እንደነበር አለማሰቡ ይሻላል፡፡ “ቪቫ ሚስተር” ሞት!...

ግን ግን ራሱ በጋሻው በዕለታዊ ሁኔታ ምናልባትም ሳያሰልስ የሚያከናውናቸውን ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚነጥሉ ስካርንና ዝሙትን የመሰሉ ተግባራትን ተራ የሥነ ምግባር ችግሮች እንጂ ሃይማኖታዊ ህፀፆች አይደሉም ብሎን ይረፍ? ምን ዓይነቱ ጉደኛ ነው ጃል! አይ ኢትዮጵያ! እንዲህ ያሉ አረሞች ይብቀሉብሽ! መጥኔ ለሕዝብሽ፡፡ መጥኔ ላንቺው ለራስሽ፡፡ እኔስ ይመስገን ፈጣሪ ጨረስኩ፡፡ ሁሉንም፡፡

## *መዝጊያ*

1. “እኔ ግን በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት ቢያገባ አመንዝራ ነው፤ [ባልዋ የፈታትንም ሴት የሚያገባ ሰው እንዲሁ አመንዝራ ነው] እላችኋለሁ፡፡” (እነበጋሻው እባካችሁን ከመጠምጠም በፊት መማርን አስቀድሙ!)

2. ወርቁ ጠፍቷል - ሚዛኑ ግን አለ፡፡ አገልጋዮች ጠፍተዋል - ቤተ ክርስቲያን ግን አለች፡፡ እረኞች የሉም - በጎች ግን እንደነገሩም ቢሆን በነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ እየዋተቱ አሉ፡፡ ተግባርና ንግግር ዐይንና ናጫ ሆነዋል፡፡ እግዚአብሔር በሰዎች አንደበት ይመለካል፤ በልቦች ውስጥ ግን ሰይጣን አለተቀናቃኝ ተንሠራቶ ተቀምጧል፡፡ ዓለም የራሷን ጉድጓድ በመማስ ላይ ትገኛለች፡፡ የሚወዳትን እየቀበረች አጥፊዋን ታፋፋለች፡፡ ዋልጌዎችን እያሳደገች ጨዋዎችንና የተማሩ ልጆቿን ታጫጫለች፤ ቀርጥፋም ትበላቸዋለች፡፡ ደናቁርት ማይማን እንዲገዟት ጓዳ ጎድጓዳዋን በረጋግዳ ትሰጣቸዋለች፡፡ የሚያራቁቷትን ታፈቅራለች፤ የሚያለብሷትንና የሚያከብሯትን ግን ታዋርዳቸዋለች፡፡ አሁን መሸሻ የለም፡፡ የምጥ መጀመሪያ፣ የዕልቂት ደወል የማሰሚያ ዘመን ነው... የሆነው ቢሆን ግን ሞትን ሣይሆን ኃጢአትን እንፍራት ፡፡

3. ይሄ የወያኔ መንግሥት ቁጥር የሚባል ነገር አያውቅም፡፡ አንዲት የ14 ዓመት ልጅ አውስትራሊያ 20 ሚሊዮን ዶላር ሸለመቻት ብሎ አወራ አሉ፡፡ይህን ያህል ነጭ ውሸት ለምን አስፈለገ? “የሌባ ዐይነ ደረቅ...” እንዲሉ ወዲ አድሓኖም “ሕጻኗ ብትሳሳት እንኳ ከርሷ ጎን መቆምን እመርጣለሁ፤ የጀመረችው ፕሮጀክት ይሣካላት” በማለት የሚያደርቀን ምን ዓይነት የባሰበት ደንቆሮ ቢሆን ነው? ለመሆኑ ኖቤልንና ሞኑ ኢብራሂምን የመሳሰሉ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ሽልማቶች ስንት እንደሚሸልሙ አያውቁ ይሆን? ይህች ሕጻን ብትሸለም ብትሸለም ከ500 ወይ ከ1000 ዶላር ሊበልጥ አይችልም - በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ ህም ሲበዛ ነው፡፡ የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ መ/ቤት እየቀመረ የሚያወጣላቸው ፍብርክ ቁጥር ትዝ አላቸውና የማይጣራ መስሏቸው ይህን የክት ቁጥር ቅንጣት ሣያፍሩ እንደፈለጉ በሚቀረሹበት ሚዲያ ለቀቁት፤ እንዴ - አማካሪ የሚባል የላቸውም? መጥኔ ለሕወሓት የወደፊት ታሪክ፡፡ እኛስ መቼም ቢሆን የጊዜ ጉዳይ እንጂ ከነዚህ ውሸታም አረመኔዎች መገላገላችን አይቀርም፤ ዕድሜ ለዕድሜ ጌታ ኅያው እግዚአብሔር፡፡ ጠብቅ - እንጠብቅ፡፡ እንደሰቀላቸው ያወርዳቸዋል - አዋርዶ፡፡

4. የራሔል ጩኸት በራማ በረከተ፡፡ ኢትዮጵያም እያነባች ናት፡፡ ልጆቿ በሁለትና በሦስት እሳቶች እየተገረፉ ዋይታና ልቅሷቸውን ለፈጣሪ እያሰሙ ይገኛሉ፡፡ ፈጣሪም በ”ዳተኝነት” ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ ትቶ - በትረ መንግሥቱንም ለሣጥናኤል አስረክቦ “የተኛ” ይመስላል፡፡ የርሱና የሰው ቀን አቆጣጠር እጅጉን የሚለያይ በመሆኑ ለፍርድ የሚጣደፍ ሆኖ አልተገኘም - ስለዚህም ይመስላል ሥጋ ወደሙን የሚፈትቱና ምሥጢረ መለኮትን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሠርጎ ገብ የዲያቢሎስ ጭፍሮች ሁሉ በጠባቡ እልፍኝ ውስጥ የሚገኘውን የጌታን ማዕድ እየናቁ ወደሰፊው አዳራሽ እየተመሙና የእግዜርን ታጋሽነት በተለይም በጠላቶቻችን በአረማውያን ዘንድ ጥያቄ ላይ እየጣሉት የሚገኙት፡፡ ከዚህ አኳያ መፍረዱ ለማይቀረው ፈጣሪ ከታጋሽነቱ ብዛት የተነሣ ብዙዎች ተስፋ እንዲቆርጡና ለዲያቢሎስ መንግሥት እንዲንበረከኩ እያደረገ እንደሆነ በመጥቀስ አምላክን የሚወቅሱ አሉ - ፈጣሪን መውቀስ የሚያዛልቅ ይመስል፡፡ “ሁሉም ለበጎ ነው” ከማለት ውጪ ለጊዜው ሌላ አማራጭ ያለ አይመስልም፡፡ አሁንና ዛሬ እኛ በብዙ እሳት እየተገረፍን ነው፡፡ የወያኔዎች ጭቆና አንዱ እሳት ነው፤ ዓለም አቀፉ የጨለማው መንግሥት በየቦታው የሚለኩሰው እሳት ሌላው ነዲድ ነው፤ በየደቂቃው እያሻቀበ የሚሄደው የኑሮ ውድነት አንዱና ለሽክም የከበደን እሳት ነው፡፡ በሥጋም በመንፈስም የተቀበረ ሕዝብ ይዘህ በአስፋልት መንገድና በሚያማምሩ ሕንፃዎች ዓለምን ማታለሉ የትም አያደርስም፤ የአንድ መቶኛ ዜጎች ንብረትም የ99 መቶኛን ዜጎች ሆድ አይሞላም፡፡ ነገር አለ! ያውጣን፡፡